## የተማሪ የስነ ምግባር ጥሰቶች

- የአካዳሚክ ታማኝነት የጎደለው ድርጊት/ ማጭበርበር ማቃጠል
- ጥቃት
- አካላዊ ጥቃቶች
- የኮምፒውተር አላግባብ መጠቀም፣መነካካት እና መተላለፍ
- አደገኛ የጦር መሳሪያዎች
- አድሎአዊ ትንኮሳ
- አለመታዘዝ
- የሚረብሽ ስነ ምግባር
- የአልኮል መጠጦችን ማሰራጨት
- ሕጋዊ ያልሆኑ ኣደገኛ ዕጾች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ነገሮች እና በሃኪም የሚታዘዙ ወይም ከሱፐር ማርከት ሊገዙ የሚችሉ መድሓኒቶች ማሰራጨት
- ማሪዋና ማሰራጨት
- መበዝበዝ፣ማስፈራራት፣ማስገደድ
- የውሸት ማስጠንቃቂያ
- የውሸት ሪፖርት
- በውሸት ማስፈራራት
- ርችቶች መተኮስ
- ርችቶች፣ፍንዳታ፣ኬሚካል እና ተቀጣጣይ መሳርያ
- ቁማር
- በግድግዳ ላይ መጻፍ
- ትንኮሳ፣ማስፈራራት ወይም የዱርዬ/የጥላቻ ቡድን እንቅስቃሴ
- ማጥቃት
- ተገቢ ያልሆነ ቋንቋ
- ተገቢ ያልሆነ መንካት
- በትምህርት ቤት ባለስልጣናት ላይ ጣልቃ መግባት
- የትምህርት ቤት ባለስልጣናትን ማስፈራራት
- የዝሙት ስነምግባር
- ተንኮል ያለው ትንኮሳ
- የንብረት ውድመት
- የተሳሳተ ውክልና
- ሌሎች ልዩ ጥፋቶች
- ህገወጥ መድሃኒቶች፣የተከለከሉ ንጥረ ነገሮች፣በሐኪም የታዘዙ ወይም ያልታዘዙ መድሃኒቶችን ይዞ መገኘት ወይም መጠቀም
- የአልኮል መጠጦችን መያዝ ወይም መጠቀም
- ማሪዋናን መያዝ ወይም መጠቀም
- የትምባሆ ምርቶች (የኤሌክትሮኒክስ ትነት መሳሪያዎች) መያዝ ወይም መጠቀም
- የተሰረቀ ንብረት መያዝ
- ዘረፋ
- ደንብ መጣስ
- የአልኮል መጠጦችን መሸጥ
- ህገወጥ መድሃኒቶች፣የተከለከሉ ንጥረ ነገሮች፣በሐኪም የታዘዙ ወይም ያልታዘዙ መድሃኒቶችን መሸጥ
- ማሪዋና መሸጥ
- ፆታዊ ጥቃት
- ፆታዊ ትንኮሳ
- ስርቆት
- የጥቃት ማስፈራሪያዎች
- መተላለፍ

### አንድ ተማሪ ደንብ ከተላለፈ ምን ይሆናል??

አንድ ተማሪ ደንብን በመጣስ በሚከሰስበት ጊዜ የስነስርዓት ኣርምጃ ከመወሰዱ በፊት በብኩሉ ያለውን እውነት ለትምህርት ቤት ሠራተኞች የማብራራት መብት አለው።ወላጅ ከትምህርት ቤት ሰራተኞች ጋር ችግሩን ለማወቅ፣መፍትሔ ለማፈላለግ ወይም ተገቢ ቅጣት ለመወሰን መገናኘት ይችላሉ።ሆኖም ግን ጥፋቱ ኣስከፊ ከሆነ ተማሪው ከትምህርት ቤት ሊታገድ ወይ ሊባረር ትችላለህ።

አንድ የትምህርት ቤት መሪ በአስቸኳይ ተማሪን እንዲያባርር በቂ ምክንያት ሊኖረው ይገባል።ሀ) ለሌሎች ተማሪዎች ወይም ለትምህርት ቤት ሰራተኞች ለግዜው ወይም ለቀጣይ አደጋ የሚያመጣ ከሆነ፤ወይም (ለ) በትምህርት ሂደት ውስጥ ቁሳዊ እና መጠነ ሰፊ የሆነ መስተጓጎል ለግዜው እና ለቀጣይ የሚያስከትል ከሆነ።አንድ ተማሪ ከትምህርት ቤት ከታገደ፣ጠቅላላ ከተባረረ ወይም በአስቸኳይ ሁኔታ ከተባረረ በ24 ውስጥ የተወሰደውን የስነስርኣት እርምጃ የሚገልጽ (ኖቲስ ኦፍ ዲሲፕሊነሪ ኣክሽን (NDA) ደብዳቤ ይደርሰዋል።

*ስለ የዲሲፕሊን ይግባኝ ሂደት አስመልክቶ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን* **discipline@seattleschools.org** *ያነጋግሩ።*

### አንድ ተማሪ በደል እየተፈጸመብኝ ነው ብሎ ብያስብስ?

ርእሰ መምህሩ ወይም ምክትል ርእሰ መምህሩ የስነስርዓት ኣርምጃ ሊወስድብህ ከወሰነ እና የተመደበው ያስነስርዓት እርምጃ ተማሪው ተገቢ ኣና ፍትሃዊ ያለሆነ ነው ብለህ ካመንክ ተማሪው ውሳኔውን መቃወም እና ይግባኝ የማለት መብት ኣለህ።የተለያዩ የይግባኝ ኣፈጻጸሞች የተማሪዎች መብት ኣና ሓላፊነቶች የሚለው ጽሑፍ ላይ ይገኛል።ይህን ጽሑፍ ከትምህርት ቤትህ፣ከዲሲፕሊን ኦፊስ በስልክ ቁጥር 206-252-0820 ወይም ከሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ዌብ ሳይት በሚቀጠልው ኣድራሻ፤ www.seattleschools.org ማግኘት ይቻላል።

### የፌደራል ከኣደንዛዥ ዕጾች ነጻ የሆኑ ትምህርት ቤቶች እና የ1989 የ ማሕበረሰቦች ድንጋጌ የተማሪዎች እና የወላጆች ማስታወቅያ

ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ሕገወጥ በሆነ መንገድ ተማሪዎች ኣልክሆል እና ኣደንዛዥ ዕጽ ትምህርት ቤት ግዚ ውስጥ፣በት / ቤት ንብረት ውስጥ፣በት / ቤት ስፖንሰር በተደረገ ትራንስፖርት ወይም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ላይ መያዝ፣መጠቀም ወይም ማከፋፈል ይከልክላል።ይህን ሕግ ማክበር የግድ ነው። ይህን ሕግ የሚጥሱ ተማሪዎች የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወሰድባቸው ይችላል።ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች የአደንዛዥ እፅ እና የአልኮል ትምህርት፣የምክር እና የመልሶ ማገገም ድጋፍን በማመቻቸት ወይም በማቅረብ በኩል ሊረዳ ይችላል።ለተጨማሪ መረጃ፣የትምህርት ቤትዎን መሪ፣የትምህርት ቤትዎን የማህበራዊ ሠራተኛ ወይም አማካሪዎን ያነጋግሩ።


የሲያትል ት/ቤቶች የቦርድ አባላት

Chandra N. Hampson
Leslie S. Harris
Brandon K. Hersey
Liza Rankin
Lisa Rivera Smith
Michelle Sarju
Vivian Song Maritz


# ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች

## የተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች

2022-2023









ዋና ሃላፊ
Dr. Brent Jones

Seattle Public Schools

## ተልዕኮ

ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ተደራሽነትን ለማረጋገጥ እና ለእያንዳንዱ ተማሪ የላቀ ትምህርት ለመስጠት የእድል ክፍተቶችን ለማስወገድ በትጋት ይሰራል።

## ራዕይ

እያንዳንዱ የሲያትል የህዝብ ት/ቤት ተማሪ ከፍተኛ ጥራት እና ዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው ትምህርት ያገኛል እና ለኮሌጅ፣ለሥራ፣እና ለማህበረሰብ ዝግጁ ሆኖ ይመረቃል ።

## የእኩልነት እና ተገዢነት ፖሊሲ:

ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ለሁሉም እኩል እና ርትዓዊ የትምህርት እና የስራ ዕድል ይሰጣል።እንዲሁም በሁሉም ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች ላይ ያለምንም የዘር፣የቀለም፣የብሔር፣ጾታ፣ሃይማኖት፣ዕድሜ፣የትውልድ ኣገር፣ሃብት እና ገንዘብ፣የአካል ጉዳተኝነት፣ጾታዊ ዝንባሌ ማለትም የሆነ ሰው የሚጠራበት ጾታ ወይም መለያ፣እርግዝና፣የጋብቻ ሁኔታ፣ኣካላዊ ቅርጽ፣የሆነ የኣእምሮ ወይም የኣካል ጉዳተኛነት ወይም በክብር የተሸኙ ወታደሮች እና ኣርበኝነት፣ወታደር መሆን ወይም የሰለጠነ መሪ ውሻ ወይም ሌላ እንስሳ በመጠቀም ልዩነት ሳያደርግ ለሁሉም ሰው እኩል ዕድል ይሰጣል።ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ለሁሉም የተመደቡለት ወይም ተወከለው የመጡ እንደ ቦይ ስካውት እና ሌሎች የወጣቶች ማህበራት እኩል ዕድል ይሰጣል።ለተማሪዎች እና ለሁሉም የማህበረሰብ ኣባላት የሚከተሉት የመ/ቤቱ ሰራተኛች ጥያቄዎችን ሊመልሱና እና የተፈጸመ መድልዎ አቤቱታዎችን ሊቀበሉ የተመደቡ ስለሆነ ከታች ከተገለፁት በደብዳቤ፣በስልክ ወይም በኢሜይል ልታገኙዋቸው ትችላላችሁ:

Seattle Public Schools MS 32-149
PO Box 34165
Seattle, WA 98124-1165

***ፆታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ ስለ የፆታዊ ኢድልዎ ጉዳዮች:***

Title IX Grievance Coordinator (206) 252-0367
title.ix@seattleschools.org

***ስለየአካል ጉዳተኝነት ኢድልዎ ጉዳዮች:***

ADA/Section 504 Grievance Coordinator
(206)252-0885
504coordinator@seattleschools.org

***ስለ ለሌሎች የኢድልዎ ጉዳዮች በሙሉ:***

Student Civil Rights, (206) 252-0306
oscr@seattleschools.org

***በአስተማሪዎች የሚቀርቡ ከአካል ጉዳተኝነት ጋር የተያያዙ ኣገልግሎቶች ወይም /እና ስለሚነሱ ቅሬታዎች፣ፆታዊ ትንኮሳን ጨምሮ:***

Chief of Human Resources
Seattle Public Schools MS 33-157
PO Box 34165
Seattle, WA 98124-1165
206-252-0024 or hreeoc@seattleschools.org

*ያነጋግሩ*




## ሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች ለማድረግ ቃል የሚገባቸው

የ እድል ልዩነቶችን ማጥበብና ለሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ልቀትን ማረጋገጥ ወቅታችን ጉዳይ ነው።

ሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች የሚከተሉትን ይገነዘባል:

- በዲስትሪክቱ ውስጥ በየዲሲፕሊን ግብረመልሶች ላይ የዘር አለመመጣጠን እንዳለ፤
- እያንዳንዱ ዲስፕሊን የሚመለከት ጉዳይ በጣም የተወሳሰበና ሊሆን ስለሚችል ሰራተኞች የተማሪዎችን ባህሪ መረዳት እንዳለባቸው፤
- ትምህርት ቤቱ የዲሲፕሊን ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ተማሪዎች፣ ቤተሰቦች እና አሳዳጊዎች ግብዓት በመስጠት ንቁ አጋሮች የመሆን መብት አላቸው፤
- በዲሲፕሊን ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የሚሳተፉ አካላት የሁኔታውን ቅለት እና ክብደት ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው፤እና
- እገዳ ተግባራዊ ሲሆን በተማሪዎች ተሳትፎ እና በምረቃ ላይ የማይካድ አሉታዊ ተጽዕኖ አለው።

## የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና የሰራተኞች ሃላፊነቶች:

የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሠራተኞች የሚከተሉትን ሓላፊነቶች

- ደህንነቱ የተጠበቀ እና ተቀባይ የሆነ የትምህርት ቤት እና የዲስትሪክት አካባቢ መፍጠር፤
- የፀረ-ዘረኝነት ድርጊቶችን የሚያበረታቱ የመማር ዕድሎችን መፈለግ፣መሳተፍ እና መከታተል፤
- ከተማሪዎች፣ከወላጆች እና ከአሳዳጊዎች ጋር አብሮ መስራት፤
- ከተማሪዎች፣ከወላጆች እና ከአሳዳጊዎች ጋር አዎንታዊ ግንኙነቶችን ማዳበር፤
- ስነምግባርን ማስተማር እና አብነት መሆን፤እና
- ከፍተኛ ጥራት ያለው እና የፀረ-ዘረኝነት ትምህርት ለተማሪዎች ማቅረብ።

ስለ የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ኃላፊነቶች በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣እባክዎን በየተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች መጽሐፍ ላይ በገጽ 8 ይመልከቱ።

## የትምህርት ቤት የጥንቃቄ እና የደህንነት አገልግሎቶች ፕሮግራም

የጥንቃቄ እና የደህንነት ሰራተኞች የትምህርት ቤቱን ደህንነት ለመጠበቅ የእያንዳንዱን ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር ይደግፋሉ።እንደ ያልተፈቀዱ አዋቂዎች ወደ ህንጻው ለመግባት መሞከር ያሉ ውጫዊ ጉዳዮች እና እንደ ተማሪዎች መጣላት ያሉ ውስጣዊ ችግሮችን ለመፍታት ሊያግዙ ይችላሉ። በሁሉም ሁኔታዎች ትኩረታቸው ከድህነት ጋር በተዛመዱ ጉዳዮች ላይ ነው። የጥንቃቄ እና የደህንነት ቡድኑ ጥሩ የትምህርት አካባቢን ለማሳደግ ለአደጋ ወይም ለደካማ ባህሪ እንደ መከላከያ ሆኖ መሥራት ፍላጎት አለው።የሕግ አስከባሪ አካላት በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ጊዜ ሊጠሩ ይችላሉ፣ለምሳሌ በግቢው ውስጥ የጦር መሳርያ ሲኖር፣ካልሆነ አብዛኛዎቹ የደህንነት ጉዳዮች ያለህግ አስከባሪ ተሳትፎ በየጥንቃቄ እና የደህንነት እና በየትምህርት ቤት አስተዳደር ቡድን ይፈታሉ።በትምህርት ቤት ውስጥ ደህንነትን ለመጠበቅ እገዛ ከፈለጉ፣ የት/ቤትዎን የደህንነት ባለሙያ፣ርእሰ መምህር፣ወይም የጥንቃቄ እና ደህንነት ቢሮ በስልክ ቁጥር 206-252-0707 ማግኘት ይችላሉ።(የቦርድ ፖሊሲ ቁጥር 4311 እና የዋና ሃላፊ የአሰራር ቁጥር 4311 SP ይመልከቱ)

## የተማሪ መብቶች

የትምህርት ማህበረሰቡ ኣባላት እንደመሆናቸው መጠን ተማሪዎች የሚከተሉት መብቶች ኣሏቸው:

- ደህንነቱ የተጠበቀ እና ተቀባይ የሆነ ትምህርት ቤት እና የመማሪያ ክፍል፤
- ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት እና የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ማግኘት፤
- መታየት፣መደመጥ እና ተሰሚነት ማግኘት፤
- ቤተሰቦቻቸውን በትምህርት ላይ መሳተፍ፤
- በየፀረ ዘረኝነት ትምህርት በንቃት መሳተፍ፤
- ተገቢ የሆነ እገዛ ማግኘት፤እና
- የእገዳ እና የመባረር ይግባኝ በ አምስት (5) የትምህርት የስራ ቀናት፣የድንገተኛ ማባረር ይግባኝ ደግሞ በሦስት (3) የትምህርት የስራ ቀናት የመታየት።

መብቶችዎን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን በየተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች መጽሐፍ ውስጥ ገጽ 10 ን ይመልከቱ።

## የተማሪ ሀላፊነቶች

ተማሪዎች እንደ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ኣባላት፣የሚከተሉትን ሀላፊነቶች መውሰድ ኣለባቸው:

- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እርዳታ መጠየቅ፤
- ሌሎችን በአክብሮት መያዝ፤
- ትምህርት መከታተል እና ለትምህርት ዝግጁ መሆን፤
- የዲስትሪክት እና የትምህርት ቤት ደንቦችን መከተል፤
- የአለባበስ ኮድ (የቦርድ ፖሊሲ ቁጥር 3224) መከተል፤እና
- ንብረትን ማክበር (የቦርድ ፖሊሲ ቁጥር 3520) ።

ተማሪዎች እንደ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ኣባላት፣የሚከተሉትን ሀላፊነቶች መውሰድ ኣለባቸው:
ኃላፊነቶችዎን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን በየተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች መጽሐፍ ላይ ገጽ 11ን ይመልከቱ።